# መንጋን በእንቁላሉ

ማንነቱን አያውቅ ፣ ታሪኩን የረሳ
በራሱ አይመካ ፣ እይታው ኮሳሳ
የሐገር በሽታ ፣ የሐገር ነቀርሳ
ምርጫው የቆሸሸ ፣ የሆነ ጥንባንሳ
ለምንም የማይበጅ ፣ ሃሳበ አንካሳ
ፖለቲካ የሚለው ፣ ኢትዮጵያን ወቀሳ ።

ከኢትዮጵያዊነት ፣ እንዲኖር ተፋትቶ
ተረት ተረት ፣ ታሪክ ፣ ቡቱቶ ዲሪቶ
በቁቤው ፣ ቅል ራስ ፣ ለዘመናት ሞልቶ
ድኩማን አድርጎት ፣ አይረታ ተሟግቶ
በአምሳሉ የፈጠረው ፣ ቦዘኔ አዘጋጅቶ
ተረኛ ነን ፣ በሚል ፣ በባዶ ቀረርቶ
አገር ልምራ ፣ ይላል ፣ መንጋውን አዝምቶ ።

የኦነጉ ቁናስ ፣ ባጅሬ ወያኔ ፣ እየተላከከ
ውሻ በቀደደው ፣ ጅብ እየሾለከ
የታሪክ ገራባ ፣ አላምጦ እያኘከ
ያልበላውን አኮ ፣ አድምቶ እያከከ
አንጎሉን እንደጨርቅ ፣ እያመነቸከ
አጥንትና ጉልጥምት ፣ እየተመለከ
ለስልጣን መቆያ ፣ አገር እያወከ
ዘወትር ጥላቻን ፣ አለ እንደሰበከ ።

እሾህ አሜኬላ ፣ የመንጋ ጥርቅም
ከጠባብ አይምሮ ፣ ከቶ አይላቀቅም
እንኳንስ ወገኑን ፣ እራሱን አያውቅም
ትላንትናም ዛሬም ፣ ሁሌም ፣ ያገር ሸክም
ከንቱ ምኞት ይዞ ፣ እይታው ቢናቅም
ካጋም ፣ መጠጋት ነው ፣ ብቻውን አይወድቅም ።

በፍርሃት ተውጠው ፣ ከእውነት የሚሸሹ
ባንሳለሁኝ ስሜት ፣ አድፈው የቆሸሹ
ዘወትር ቢያልሙ ፣ ሁሌም በትንሹ
አልቅትና መዥገር ፣ በሐገር የፈሉ
በአብይ መሪነት ፣ የተኮለኮሉ
ካፍንጫ የራቀ ፣ ማየት ያልታደሉ
ባገር ሰላም የለም ፣ ወድቀው ሳይጣሉ
መቅጨት በጊዜ ነው ፣ መንጋን በእንቁላሉ ።

ታዛቢው

September 26, 2019